# የተሻሻለ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ምልመላና ምርጫ

# የአሰራር ደንብ

ሕዳር 2018 ዓ.ም.
አዲስ አበባ

ጎሕ ቤቶች ባንክ
GOH BETOCH BANK

# ማዉጫ


ክፍል አንድ ........ 1
ጠቅላላ ድንጋጌዎች ........ 1
1. መግቢያ ........ 1
2. አጭር ርዕስ ........ 1
3. ትርጓሜ ........ 1
4. ስለጾታዊ አገላለጽ ........ 2
ክፍል ሁለት ........ 3
የቦርድ አባላት መምረጫ መርሆችና መስፈርቶች ........ 3
5.1. የቦርድ አባላት ምርጫ መርሆዎች ........ 3
5.2. የምርጫ መስፈርቶች- ለሁሉም ዳይሬክተሮች ........ 3
5.2.1. ታማኝነት (integrity) ........ 3
5.2.2. የፋይናንስ ጤናማነት ........ 4
5.2.3. ሌሎች መመዘኛዎች ........ 4
5.3. የምርጫ መስፈርቶች-ለገለልተኛ ዳይሬክተሮች ........ 4
5.4. የምርጫ መስፈርቶች-ገለልተኛ ላልሆኑ ዳይሬክተሮች ........ 5
5.5. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ስብጥር ........ 5
ክፍል ሦስት ........ 6
ከቦርድ ምርጫ ጋር በተያያዘ የባንኩ አካላት ግዴታና ኃላፊነት ........ 6
6.1. የጠቅላላ ጉባኤ ግዴታና ኃላፊነት ........ 6
6.2. የዳይሬክተሮች ቦርድ ግዴታና ኃላፊነነት ........ 6
6.3. የአስመራጭ ኮሚቴ ........ 7
6.3.1. ስለኮሚቴዉ መቋቋም ........ 7
6.3.2. የኮሚቴዉ ግዴታ እና ኃላፊነት ........ 7
6.4. የማህበሩ ጸሐፊ ግዴታና ኃላፊነት ........ 8
ክፍል አራት ........ 9

የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ጥቆማና ምርጫ አፈጻጸም 9
7. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ዕጩዎች ጥቆማ ሒደት 9
8. ሥራ ላይ ያሉ የቦርድ አባላት ዳግም መመረጥ 10
9. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት የምርጫ ሒደት 11
10. የምርጫ ድምፅ ቆጠራና ውጤት ስለማሳወቅ 11
11. የአስመራጭ ኮሚቴ የሥራ ማጠናቀቂያ ጊዜ 13
ክፍል አምስት 13
ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች 13
12. የሌሎች ሕጎች ተፈፃሚነት 13
13. የጸደቀውን የአሰራር ደንብ ስለማክበር 13
14. የአሰራር ደንቡን ስለማሻሻል 13
15. ስለተሻረ የአሰራር ደንብ 13
16. ደንቡ የሚፀናበት ቀን 13

# ክፍል አንድ
# ጠቅላላ ድንጋጌዎች

## 1. መግቢያ

የኢትዮጵያ የንግድ ሕግ አንቀጽ 298 የአንድ አክሲዮን ማህበር የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት በማህበሩ የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ እንደሚመረጡ ይደነግጋል። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያዎችም የአንድ ባንክ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት በባንኩ ባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ እንደሚመረጡ ይገልጻሉ። የባንኩ የመመስረቻ ጽሑፍም የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን የመምረጥና የመሻር ስልጣን የባንኩ ባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ መሆኑን ይጠቅሳል።

የዳይሬክተሮች ቦርድ አስፈላጊዉን የኮርፖሬት አስተዳደር የማስፈን፣ የመምራትና የባንኩን ሥራ የመቆጣጠር ቁልፍ ሚና ያለዉ በመሆኑ ብቃትና ችሎታ ያላቸው ዳይሬክተሮች የሚመረጡበትን ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ነዉ። የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ምልመላና ምርጫ ሒደት ግልፅነት የተላበሰ እንዲሆን በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የባንክ ኮርፖሬት አስተዳደር (Bank Corporate Governace) መመሪያ ቁጥር SBB/91/2024 የተገለጸ ሲሆን ይህንን ለመፈጸም በጠቅላላ ጉባኤ የጸደቀ "የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ምልመላ እና ምርጫ አፈጻጸም አሰራር ደንብ" እንዲኖር ይጠይቃል።

ስለሆነም ከዳይሬክተሮች ቦርድ ምርጫ ጋር በተያያዘ ሊሟሉ ስለሚገባቸዉ ሁኔታዎች በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪዎች የተቀመጡትን ለማሟላት እንዲሁም ነባሩ የባንካችን የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ምልመላና ምርጫ ማስፈጸሚያ የአሰራር ደንብ ከወጣ በኋላ ያሉትን ለዉጦች በደንቡ ውስጥ በማካተት ደንቡን ማሻሻል በማስፈለጉ ይህ የተሻሻለ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ምልመላና ምርጫ የአሰራር ደንብ እንደሚከተለዉ በአራተኛዉ የባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ጸድቋል።

## 2. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ **"የተሻሻለ የጎሕ ቤቶች ባንክ አ.ማ. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ምልመላ እና ምርጫ የአሰራር ደንብ"** ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## 3. ትርጓሜ

የቃሎቹ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጣቸዉ ካልሆነ በስተቀር በዚህ የአሰራር ደንብ ውስጥ ያሉት ቃላት ከዚህ በታች የተሰጣቸውን ትርጓሜዎች ይይዛሉ።

3.1. "ባንክ" ማለት ጎሕ ቤቶች ባንክ አ.ማ. ማለት ነው።

3.2. "ቦርድ" ማለት የባንኩ የዳይሬክተሮች ቦርድ ነው።

3.3. "ዳይሬክተር" ወይም "የቦርድ አባል" ማለት የባንኩ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል ነው።

3.4. "ገለልተኛ ዳይሬክተር" ማለት በማንኛውም የባንኩ የአስተዳደር ሥራ ውስጥ የማይሳተፍ፣ ከባንኩ ጋር የሞያ

አገልግሎት፣ የንግድ ወይም የሌላ ዓይነት ሥራ ግንኙነት የሌለዉ ዳይሬክተር ሆኖ ነጻ እና ሚዛናዊ አስተያየቱን ከሚያዛባ ማንኛውም ዐይነት ውስጣዊ፣ ውጫዊ እና ሌሎችም ተፅዕኖዎች ነጻ የሆነ እና የባንኩ አክሲዮን ባለቤት ያልሆነ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል ነው።

3.5. “ዋና ሥራ አስፈጻሚ” ማለት የባንኩን የዕለት ተዕለት ሥራዎች በበላይነትና በዋና ኃላፊነት የመምራት ሥልጣን የተሰጠው ሰው ነው።

3.6. "የማህበሩ ጸሐፊ" ማለት በባንኩ የዳይሬክተሮች ቦርድ የሚሾምና ተጠሪነቱ ለዋና ሥራ አስፈጻሚው የሆነ ኃላፊነትና ተግባሩ አግባብነት ባላቸዉ ሕጎች መሠረት የተወሰነ ሰው ነው።

3.7. “ሠራተኛ” ማለት በባንኩ ውስጥ በማናቸውም የሥራ ኃላፊነት ወይም የሥራ መደብ ላይ ተሹሞ ወይም በቋሚነት ተቀጥሮ በባንኩ የዕለት ተዕለት ሥራዎች የሚሳተፍ ሰው ማለት ነው።

3.8. “ጠቅላላ ጉባዔ” ማለት የባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ማለት ነው።

3.9. “ተደማጭነት ያለው ባለአክሲዮን” ማለት ከባንኩ ጠቅላላ የተፈረመ ካፒታል ውስጥ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ሁለት በመቶና ከዚያ በላይ የአክሲዮን ድርሻ የያዘ ሰው ነው።

3.10. “ተደማጭነት የሌለው ባለአክሲዮን” ማለት ከባንኩ ጠቅላላ የተፈረመ ካፒታል ውስጥ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ከሁለት በመቶ በታች የአክሲዮን ድርሻ የያዘ ሰው ነው።

3.11. “ኮሚቴ” ወይም “አስመራጭ ኮሚቴ” ማለት ጠቅላላ ጉባኤው በሚደረግበት ዕለት የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ምርጫን ለማካሄድ ጥቆማ የሚቀበልና የሚያስመርጥ በጉባኤው ዕለት የሚመረጥ ጊዜያዊ ኮሚቴ ነው።

3.12. “ቁልፍ ችሎታ/Core Competency” ማለት ከባንክ ሥራ ወይም ከፋይናንስ ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ተብለው በኢትየጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ ላይ የተገለጹ የትምህርት ዝግጅትና የሥራ ልምድ ማለት ነው።

3.13. “አቻ የትምህርት ደረጃ ” ማለት ከውጭ ሀገር ተቋም የተገኘ የትምህርት ማስረጃ በኢትዮጵያ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ከሚሰጡ የትምህርት ደረጃዎች አንጻር ተመዝኖ አቻ ተደርጎ የተሰጠ የትምህርት ደረጃ ማለት ነው።

3.14. “የመጀመሪያ ደረጃ ዝምድና” ማለት ባል ወይም ሚስት፣ ልጅ እና የባል/የሚስት ወላጆች ማለት ነው።

3.15. “የፋይናንስ ተቋማት” ማለት ባንክ፣ ኢንሹራንስ፣ አነስተኛ የፋይናንስ ተቋማትና ሌሎች በባንክ ሥራ አዋጅና በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያዎች መሠረት የፋይናንስ ተቋም የሚባሉትን ሁሉ ያጠቃልላል።

## 4. ስለጾታዊ አገላለጽ

በተለየ ሁኔታ ካልተመላከተ በስተቀር በወንድ ጾታ የተገለጸው ሁሉ ለሴት፣ በነጠላ ቁጥር የተጠቀሰው ለብዙ ያገላግላል።

# ክፍል ሁለት
# የቦርድ አባላት መምረጫ መርሆችና መስፈርቶች

## 5.1. የቦርድ አባላት ምርጫ መርሆዎች

5.1.1. የቦርድ አባላት ምርጫ የባለአክሲዮኖችን ሁለንተናዊ ተሳትፎ እና ፍትሐዊ ውክልና በሚያረጋግጥ መልኩ ግልጽ የዕጩዎች ጥቆማና ምርጫ ሂደትን በመከተል ይደረጋል፡፡

5.1.2. መልካም ተቋማዊ ባህል እና እሴት እንዲፈጠር የድርሻቸዉን ሊወጡ የሚችሉ የቦርድ አባላት እንዲመረጡ ይደረጋል፡፡

5.1.3. የባንኩን ሥራ ጤናማና ተገቢ በሆነ ሁኔታ ለመምራት የሙያ ብቃት፣ ዕውቀት፣ክህሎት እና ልምድ ያላቸዉ የቦርድ አባላት እንዲመረጡ ጥረት ይደረጋል፡፡

## 5.2. የምርጫ መስፈርቶች- ለሁሉም ዳይሬክተሮች

ማንኛውም ዕጩ ለቦርድ አባልነት ሊጠቆም ወይም ሊመረጥ የሚችለው ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መስፈርቶች አሟልቶ ሲገኝ ነው፡፡

### 5.2.1. ታማኝነት (integrity)

ማንኛውም ዳይሬክተር፦

1. በኢትዮጵያም ሆነ በሌላ ሀገር ሕዝብን ከማጭበርበር ለመጠበቅ በወጡ ሕጎች በወንጀል ተከሶ ጥፋተኛ ያልተባለ መሆን አለበት፡፡

2. እራሱ ወይም የጎላ ተጽዕኖ ፈጣሪ የሆነበት ድርጅት በሚመለከተው የመንግስት አካል መረጃ ተጠይቆ የከለከለ፣ የተሳሳተ የፋይናንስ ወይም ሌላ መግለጫ ያቀረበ፣ የተቆጣጣሪውን አካል ትዕዛዝ በእምቢተኝነት ያልተቀበለ፣ የማስተካከያ እርምጃዎችን ያላከበረ መሆን የለበትም፡፡

3. እራሱ ወይም የጎላ ተጽዕኖ ፈጣሪ የሆነበት ድርጅት በተቆጣጣሪው አካል፣ በሚመለከተው የሙያ ማህበር ወይም የዳኝነት ሥልጣን ባለዉ አካል ከዕምነት ማጉደል፣ ከማጭበርበር እና ሌላ ተያያዥ የፋይናንስ ወንጀል ጋር በተያያዘ ጥፋተኛ ሆኖ የተቀጣ፣ በሥነ ምግባር ጥሰት የተቀጣ ወይም ተግሣጽ የተሰጠው መሆን የለበትም፡፡

### 5.2.2. የፋይናንስ ጤናማነት

ማንኛውም ዳይሬክተር፡-

1. በኢትዮጵያ ወይም በሌላ ሀገር እራሱ፣ ወይም የራሱ ሚና መታየት ያለበት መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ራሱ ዳይሬክተር ወይም ዋና ሥራ አስፈጻሚ ወይም ከፍተኛ ሥራ አስፈጻሚ ወይም ባለቤት በሆነበት ድርጅት ላይ የመክሰር ሂደት ያስጀመረ ወይም መክሰሩ የታወጀበት፤ የራሱ ወይም የድርጅቱ ንብረት የተወረሰበት፣ ንብረቱ በንብረት አጣሪ ሥር እንዲተዳደር የተደረገበት ወይም የባንክ ብድር ባለመክፈሉ ንብረቱ በሐራጅ የተሸጠበት መሆን የለበትም።
2. እራሱ ወይም እራሱ ዳይሬክተር ወይም ዋና ሥራ አስፈፃሚ ወይም ከፍተኛ ሥራ አስፈፃሚ ወይም ባለቤት የሆነበት ድርጅት የባንክ ወይም ሌሎች ብድሮችን ወይም ግብር ያልከፈለ መሆን የለበትም።
3. እራሱ፣ ወይም እራሱ ዳይሬክተር ወይም ዋና ሥራ አስፈፃሚ ወይም ከፍተኛ ሥራ አስፈፃሚ ወይም ባለቤት የሆነበት ድርጅት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የቦርድ አባልነቱን ከማፅደቁ በፊት ባሉት ሁለት ዓመታት በባንክ ወይም በማንኛውም የፋይናንስ ተቋም የተበላሸ ብድር የሌለበት መሆን አለበት።
4. በባንክ ሂሳቡ ውስጥ በቂ ስንቅ ሳይኖረው አግባብነት ያለውን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ በመጣስ የቼክ ክፍያ ፈጽሞ የባንክ ሂሳቡ ተዘግቶ ተመልሶ ያልተከፈተለት መሆን የለበትም።

### 5.2.3. ሌሎች መመዘኛዎች

1. ሀቀኛ፣ ጠንቃቃ፣ መልካም ዝና እና መልካም ሥነ ምግባር ያለው፤
2. ከአራት በላይ በሆኑ ሌሎች ድርጅቶች ውስጥ በቦርድ ዳይሬክተርነት እየሠራ ያልሆነ፤
3. የሌላ ባንክ ሠራተኛ ያልሆነ፤
4. በቂ ጊዜ በመመደብ ሥራውን ለመስራት ወይም ኃላፊነቱን ለመወጣት የሚችል፣
5. በቦርድ አባልነት ለማገልገል ፈቃደኛ የሆነ፤
6. አግባብነት ባለው ሕግ መሠረት የተደነገጉ ሌሎች መስፈርቶችን የሚያሟላ፤
7. በተጨማሪም በቦርዱ ውስጥ የጾታ ስብጥር እንዲኖር ቢያንስ ሁለት ሴቶች የቦርድ አባል ሆነው መመረጥ አለባቸው።

## 5.3. የምርጫ መስፈርቶች-ለገለልተኛ ዳይሬክተሮች

አግባብነት ባላቸው ሕጎችና መመሪያዎች የተመለከቱ ሌሎች መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆነው ገለልተኛ ዳይሬክተር ሆኖ የሚጠቆምና የሚመረጥ ሰዉ ቢያንስ የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት አለበት።

5.3.1. ከባንኩ ጋር የሙያ፣ የንግድም ሆነ የሌላ ሥራ ግንኙነት የሌለዉ፣የባንኩ ከፍተኛ አመራር አባል ያልሆነና በባንኩ የዕለት ተዕለት ሥራ ውስጥ ተሳትፎ የሌለዉ፤

5.3.2. በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የባንኩ ባለአክሲዮን ያልሆነ፣

5.3.3. ከባንኩ ባለአክሲዮን፣ ዳይሬክተር፣ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ወይም ከፍተኛ ሥራ አስፈጻሚ ጋር የመጀመሪያ ደረጃ የሥጋ ዝምድና ወይም የጋብቻ ዝምድና የሌለዉ፣ ወይም ተጋቢ ያልሆነ፤

5.3.4. ከባንኩ ጋር የውል ግዴታ ያለበት ድርጅት ውስጥ ባለድርሻ፣ ዳይሬክተር፣ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ወይም ከፍተኛ የሥራ መሪ ያልሆነ፣

5.3.5. ከፍርድ ቤት ውጭ ያለዉን ጨምሮ በማናቸዉም ያለመግባባት መፍቻ ሒደቶች በባንኩ፣ በእናት ኩባንያዉ ወይም በተቀፅላዉ ላይ በቀረቡ ጉዳዮች አንዱን ወገን ወክሎ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በክርክሩ ያልተሳተፈ፣

5.3.6. እውቅና ካለው ከፍተኛ የትምህርት ተቋም የሁለተኛ ዲግሪ ወይም አቻ የትምህርት ደረጃ ያለው፤

5.3.7. የተማረዉ ትምህርት ከባንክ ሥራ፣ ከሒሣብ ሥራ/አያያዝ፣ ከኦዲት ሥራ፣ ከፋይናንስ፣ ከሥራ አመራር፣ ከኢኮኖሚክስ፣ ከሕግ፣ከቴክኖሎጂ እና ከተያያዥ የሙያ ዘርፎች የሆነ፤

5.3.8. በፋይናንስ የሥራ ዘርፍ ወይም ከፋይናንስ ሥራ ዘርፍ ጋር በተያያዘ በማስተማር፣ በማማከር፣ ወይም በኦዲት ሥራ ወይም በስጋት አመራር (risk management) ወይም ተያያዥነት ባለዉ የሙያ መስክ ቢያንስ 10 ዓመት የሥራ ልምድ ያለው፤

## 5.4. የምርጫ መስፈርቶች-ገለልተኛ ላልሆኑ ዳይሬክተሮች

5.4.1. እውቅና ካለው ከፍተኛ የትምህርት ተቋም ቢያንስ የመጀመሪያ ዲግሪ ወይም አቻ የትምህርት ደረጃ ያለው፤

5.4.2. በባንክ ሥራ፣ በስጋት አመራር(risk management) በፋይናንስ፣ በሒሣብ ሥራ/አያያዝ፣ በአስተዳደር (leadership)፣ በኢኮኖሚክስ፣ በሕግ፣በሥራ አመራር፣ በኦዲትንግ፣ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ወይም በኢንቨስትመንት ማኔጅመንት ወይም በተመሳሳይ የሙያ ዘርፎች የተመረቀና ቢያንስ ሰባት ዓመት የሥራ ልምድ ያለው፤

5.4.3. ኃላፊነት በጎደለው ወይም በግዴለሽ የሥራ አመራር፣ በማጭበርበር ወይም በሕገወጥ የንግድ ሥራ ምክንያት በከሰረ ወይም ዕዳ መክፈል ባልቻለ ሌላ ሰው በተደረገ የገንዘብ ድጋፍ አክሲዮን ያልገዛ እና

5.4.4. የቦርድ አባላት ምርጫ ከሚደረግበት ዕለት ሁለት ዓመታት በፊት ባለአክሲዮን ሆኖ የተመዘገበ፤

## 5.5. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ስብጥር

የባንኩ የዳይሬክተሮች ቦርድ፡-

5.5.1. ሁለቱንም ጾታ የያዘ መሆን አለበት።

5.5.2. ቢያንስ ሁለት ሴት ዳይሬክተሮች ሊኖሩት ይገባል።

5.5.3. ኢትዮጵያዊ ያልሆኑና መኖሪያቸዉን በኢትዮጵያ ያደረጉ የውጭ ዜጎችን ሊያካትት ይችላል።

5.5.4. በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ መሠረት በተለያዩ የሙያ ዘርፎች አግባብነት ያለዉ ልምድ፣ ዕውቀት እና ክህሎት ያላቸዉ አባላት እንዲኖሩት ጥረት ይደረጋል።

5.5.5. ተደማጭነት በሌላቸዉ ባለአክሲዮኖች ብቻ የሚጠቆሙና የሚመረጡ፣ በሁሉም ባለአክሲዮኖች የሚጠቆሙና የሚመረጡ እና ሥራ ላይ ባለዉ ቦርድ የሚመለመሉና በሁሉም ባለአክሲዮኖች የሚመረጡ አባላት ይኖሩታል።

5.5.6. የማህበሩ ጸሐፊ የቦርድ አባል መሆን የማይችሉ ሲሆን ዋና ሥራ አስፈጻሚ እና ከፍተኛ ሥራ አስፈጻሚዎችን ጨምሮ የባንኩ ሠራተኞች የቦርድ አባል መሆን ይችላሉ። ነገር ግን የባንኩ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል የሚሆኑ የባንኩ ሠራተኞች ቁጥር ከሁለት ሊበልጥ አይችልም።

## ክፍል ሦስት
## ከቦርድ ምርጫ ጋር በተያያዘ የባንኩ አካላት ግዴታና ኃላፊነት

### 6.1. የጠቅላላ ጉባኤ ግዴታና ኃላፊነት

ከዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ምርጫ ጋር በተያያዘ የባንኩ ጠቅላላ ጉባኤ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል።

6.1.1. አግባብነት ባላቸዉ ሕጎች የተቀመጡ የብቃትና የተስማሚነት መስፈርቶችን ከሚያሟሉ ዕጩዎች መካከል የቦርድ አበላትን መምረጥ፤

6.1.2. ብቁ፣ ዕምነት የሚጣልባቸዉ፣ ለባንኩ ተጨማሪ እሴት የሚፈጥሩ እና ተቋማዊ መልካም አስተዳደር (corporate governance) እንዲሰፍን አስተዋፅኦ የሚያደርጉ የቦርድ ዕጩዎችን መምረጥ፤

6.1.3. የባንኩን የዳይሬክተሮች ቦርድ አበላት ምልመላና ምርጫ አፈጻጸም የአሰራር ደንብ ማፅደቅ፣ ማሻሻል፤

6.1.4. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን ጥቆማ የሚቀበልና የሚያስመርጥ አስመራጭ ኮሚቴ መምረጥ፣

6.1.5. ከሚመረጡ የቦርድ አባላት ውስጥ ቢያንስ ሁለት ሴት የቦርድ አባላትን መምረጥ፤

### 6.2. የዳይሬክተሮች ቦርድ ግዴታና ኃላፊነት

በሥራ ላይ ያለዉ ቦርድ፡ -

6.2.1. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ምልመላና ምርጫ የአሰራር ደንብን ለጠቅላላ ጉባኤው ያቀርባል፣ ሲጸድቅ ሥራ ላይ መዋሉን ያረጋግጣል፤

6.2.2. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ምርጫ በሚደረግበት ጠቅላላ ጉባኤ ላይ የአስመራጭ ኮሚቴ ምርጫን የጠቅላላ ጉባኤው ቀዳሚው አጀንዳ እንዲሆን ያደርጋል፤

6.2.3. የአስመራጭ ኮሚቴን ያስመርጣል፤

6.2.4. የቦርዱ የምልመላና የጥቅማጥቅም ኮሚቴ የመለመላቸዉንና በዕጩነት ያቀረባቸዉን ዕጩ ገለልተኛ የቦርድ አባላት የብቁነትና የተገቢነት መስፈርቶችን የሚያሟሉ መሆኑን ያረጋግጣል፤

6.2.5. በቦርዱ የምልመላና የጥቅማጥቅም ኮሚቴ ተመልምለው በዕጩነት የቀረቡትንና ቦርዱ ያጸደቃቸውን ዕጩ ገለልተኛ የቦርድ አባላት ዝርዝር ለአስመራጭ ኮሚቴው ያስረክባል፡፡

6.2.6. ባለአክሲዮኖች ድምፅ የሚሰጡባቸውን የድምፅ መስጫ ካርዶች/ወረቀቶች እና የድምፅ መስጫ ሳጥን/ኮሮጆ/ ወይም በቴክኖሎጂ የታገዘ አሰራር መዘጋጀቱን ያረጋግጣል፡፡

## 6.3. አስመራጭ ኮሚቴ

### 6.3.1. ስለኮሚቴዉ መቋቋም

1. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን ምርጫ ለማድረግ በተጠራ ጠቅላላ ጉባኤ ላይ የቦርድ አስመራጭ ኮሚቴ በጠቅላላ ጉባኤዉ የሚመረጥ ይሆናል፡፡
2. ለኮሚቴዉ አባላት ምርጫ በቅድሚያ 10 ዕጩዎች በጥቆማ እንዲቀርቡ ይደረጋል፤ ከዚያም ለእያንዳንዱ ዕጩ በሚደረግ የድምፅ አሰጣጥ ከፍተኛ ድምፅ ያገኙ 5 ዕጩዎች የኮሚቴዉ አባላት ሆነዉ ይመረጣሉ፡፡
3. የኮሚቴው አባላት ምርጫ በድምጽ መስጫ ወረቀት/ሳጥን ወይም በዲጂታል ቴክኖሎጂ ወይም በሌላ ማናቸውም መንገድ በሚከናወን የድምጽ አሰጣጥ ሥርዓት ይከናወናል፡፡
4. የኮሚቴዉ አባል ሆኖ ለመመረጥ፡-

   ሀ) ባለአክሲዮን የሆነ፣

   ለ) የባንኩ ሠራተኛ ያልሆነ፣

   ሐ) ቢያንስ የሁለተኛ ደረጃ ወይም አቻ የትምህርት ደረጃ ያለዉ፣

   መ) በእምነት ማጉደል ወይም በማጭበርበር የወንጀል ድርጊት ተከሶ በፍርድ ቤት ጥፋተኛ ያልተባለ፤

   ሠ) በቦርድ አባልነት ለመመረጥ የማይፈልግ፤

   ረ) በሥራ ላይ ያለዉ ቦርድ አባል ያልሆነ መሆን አለበት፡፡
5. ከኮሚቴዉ አባላት መካከል ቢያንስ ሁለቱ ተደማጭነት የሌላቸዉ ባለአክሲዮኖች መሆን አለባቸዉ፡፡
6. ኮሚቴው ከአባላቱ መካከል የኮሚቴውን ሰብሳቢ ይመርጣል፡፡ ኮሚቴው እንደአስፈላጊነቱ የሥራ ክፍፍል ሊያደርግ ይችላል፡፡

### 6.3.2. የኮሚቴዉ ግዴታ እና ኃላፊነት

1. የዕጩ የቦርድ አባላትን የጥቆማና የምርጫ ሂደት በበላይነት ይመራል፡፡

2. ዕጩ የቦርድ አባላት ምርጫ መስፈርቶችን ለጉባኤው ያሳውቃል፤
3. ዕጩ የቦርድ አባላትን ጥቆማ ይቀበላል፤ ያስመርጣል፤
4. በምድብ የተከፋፈለ የጥቆማና የምርጫ አካሔድን ተከትሎ የቦርድ አባላትን ያስመርጣል። እነዚህም፡-

   ሀ) **ምድብ 1** ተደማጭነት በሌላቸዉ ባለአክሲዮኖች ብቻ የሚጠቆሙና የሚመረጡ ተደማጭነት የሌላቸዉ ዕጩዎች፣

   ለ) **ምድብ 2** በሁሉም ባለአክሲዮኖች የሚጠቆሙና የሚመረጡ ዕጩዎች፤

   ሐ) **ምድብ 3** ሥራ ላይ ባለዉ ቦርድ ተመልምለው የሚቀርቡና በሁሉም ባለአክሲዮኖች የሚመረጡ ዕጩ ገለልተኛ የቦርድ አባላት።
5. ባለአክሲዮኖች ራሳቸውን የመጠቆም መብት እንዳላቸው ለጉባኤው ያሳውቃል።
6. የቦርድ አባላት ጥቆማና ምርጫ የሙያና የጾታ ስብጥርን ያሟላ መሆኑን ያረጋግጣል።
7. የጥቆማና የምርጫው ሂደት አሳታፊ፣ ፍትሀዊና ታዓማኒነት ያለው እንዲሆን ያደርጋል።
8. የምርጫ ውጤት ያሳዉቃል፤
9. የቦርድ አባላት ምርጫ በጠቅላላ ጉባኤዉ ከተከናወነ እና ውጤቱ ይፋ ከተደረገ በኋላ የተመራጩችንና የተጠባባቂዎችን ስም ዝርዝርና ያገኙትን ውጤት፣ ድምጽ የተሰጠባቸውን ወረቀቶች፣ ስራ ላይ ያልዋሉ እና ውድቅ የተደረጉ የድምጽ መስጫ ወረቀቶችን እና ሌሎች ቁሳቁሶችን እንዲሁም የተመራጩችንና እንዲሁም የተጠባባቂዎችን የሰነድ መረጃዎች ለማህበሩ ፀሐፊ ያስረክባል።

## 6.4. የማህበሩ ጸሐፊ ግዴታና ኃላፊነት

6.4.1. የቦርድ አባላት ምርጫ ከሚደረግበት ቀን አንድ ወር ቀደም ብሎ ዕጩ የቦርድ አባላት ጥቆማና ምርጫ መስፈርቶችን ተደራሽ በሆነ የመገናኛ ዘዴ በበቂ ሁኔታ ለባለአክሲዮኖች ያሳዉቃል።

6.4.2. በጠቅላላ ጉባኤ ዕለት ለቦርድ አባላት ምርጫ የሚዉሉ ቁሳቁሶች (ለምሳሌ፡- የድምፅ መስጫ ወረቀት፣ የድምጫ መስጫ ሳጥን) እንዲዘጋጁ ያደርጋል፤ መዘጋጀታቸዉንም ያረጋግጣል፤

6.4.3. ከምርጫው ጋር በተያያዘ ስራ የሚያግዙ ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች ወይም ቴክኖሎጂ(ካለ) መመደቡን ያረጋግጣል፤

6.4.4. ከኮሚቴዉ ጋር በመሆን የተመደቡትን ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች ያስተባብራል፤

6.4.5. ለቦርድ አባልነት የተመረጡ ዕጩዎች ምርጫ እንዲጸድቅ አግባብነት ያላቸዉን ሰነዶች ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ያቀርባል።

## ክፍል አራት

## የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ጥቆማና ምርጫ አፈጻጸም

### 7. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ዕጩዎች ጥቆማ ሒደት

ኮሚቴዉ፡-

7.1. ጥቆማ ከመቀበሉ በፊት የምርጫ መስፈርቶቹን በተመለከተ ለባለአክሲዮኖች ገለጻ ያደርጋል፤

7.2. ከባንኩ ሠራተኞች መካከል ከሁለት ሰዉ በላይ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል ሆነዉ ሊመረጡ እንደማይችሉ ያሳዉቃል፡፡

7.3. የሚቀበለዉ የዕጩዎች ጠቅላላ ቁጥር የቦርድ አባላት ቁጥር እጥፍ ሲሆን ለእያንዳንዱ ምድብ የሚቀበለዉ የዕጩዎች ቁጥርም የየምድቡ የቦርድ አባላት ቁጥር እጥፍ ይሆናል፡፡

7.4. መስፈርቶቹን የሚያሟሉ ዕጩዎችን ጥቆማ በሚከተለው ቅደምተከትል መሠረት በየምድቡ ይቀበላል፡፡ ይኸውም፡-

7.4.1. **ምድብ 1** ተደማጭነት በሌላቸዉ ባለአክስዮኖች የሚጠቆሙ ተደማጭነት የሌላቸዉ ባለአክሲዮን የሆኑ ዕጩዎች፤

7.4.2. **ምድብ 2** በሁሉም ባለአክሲዮኖች የሚጠቆሙና የሚመረጡ ዕጩዎች፤

7.4.3. **ምድብ 3** የገለልተኛ ዳይሬክተሮች ዕጩዎችን ዝርዝር ከትምህርትና የሥራ ልምድ ዘገባ ጋር ከቦርዱ ይቀበላል፡፡

7.5. ለምድብ 1 እና ለምድብ 2 ዕጩዎችን የሚጠቁሙ ባለአክሲዮኖች ስለሚጠቁሟቸው ዕጩዎች ቢያንስ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መረጃዎች መግለጽ እንደሚኖርባቸዉ ይገልጻል፤

7.5.1. ሙሉ ስም፤

7.5.2. የትምህርት ደረጃ፤

7.5.3. የሥራ ልምድ፤

7.5.4. ተጠቋሚው ያለውን ወቅታዊ ሥራና ኃላፊነት እና

7.5.5. ሌሎች የመምረጫ መስፈርቶችን የሚያሟላ ስለመሆኑ፤

7.6. በምድብ 1 እና በምድብ 2 ተጠቋሚዎች ላይ ድጋፍ ወይም ተቃውሞ ስለመኖሩ ጉባኤውን ይጠይቃል፡፡ ተቃውሞ ካለ ከመምረጫ መስፈርቶች አኳያ በመመርመር ኮሚቴው ተገቢ ነው ያለውን ውሳኔ ይወስናል፡፡

7.7. ነባር የቦርድ አባላት በዚህ የአሰራር ደንብ አንቀጽ 8 ስር በተደነገገው አግባብ ዳግም ለመመረጥ ሊጠቆሙ እንደሚችሉ ለጉባኤዉ ይገልጻል፡፡

7.8. በጥቆማ ወቅት የጠቋሚዎች ስምና የአክሲዮን መጠን መገለጽ እንዳለበት ለጉባኤዉ ያስረዳል፣ እያንዳንዱን ዕጩ

የትኛው ባለአክሲዮን እንደጠቆመው የሚያሳይ መረጃ ይይዛል፡፡

7.9. ከቦርዱ የቀረበለትን የገለልተኛ ዕጩዎች የፆታ ስብጥር ግምት ውስጥ በማስገባት አነስተኛዉ የሴቶች ቁጥር እንዲሟላ ወይም ከተቻለም ቁጥራቸውን ከፍ ለማድረግ መስፈርቱን የሚያሟሉ ሴቶች እንዲጠቆሙ ያደርጋል፡፡

7.10. በጥቆማው ሒደት የተጠቋሚዎች የሙያና ክህሎት ስብጥር እንዲኖር ለማድረግ በሚያስችል አግባብ ጥቆማ እንዲሰጥ ያደርጋል፡፡

7.11. የአስመራጭ ኮሚቴ አባላት ለቦርድ አባልነት ሊጠቆሙ እንደማይችሉ ለጉባኤዉ ያሳዉቃል፡፡

7.12. በእጩነት የተጠቆመው ባለአክሲዮን የሕግ ሰውነት ያለው (ተቋም) በሚሆንበት ጊዜ፤ የሚወከለው የተፈጥሮ ሰዉ እና ተቋሙ የዳይሬክተሮች ቦርድ መስፈርቶችን የሚያሟሉ ስለመሆኑ እንዲገለፅ ይደረጋል፤ተቋሙ በጉባኤዉ ላይ ተወካዩን ከላሳወቀ ፣ ተወካዩ በሚመደብበት ጊዜ የብቁነትና የተገቢነት መመዘኛዎችን የሚያሟላ መሆኑ የሚታይ ይሆናል፡፡

7.13. በዕጩነት የቀረቡት ሰዎች ብዛት በዚህ የአሠራር ደንብ ከተቀመጠው ቁጥር በታች ከሆነ ወይም በዕጩነት የቀረቡት ሰዎች በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የተቀመጡትን መስፈርቶች የማያሟሉ ከሆኑ የዕጩዎቹ ብዛት መስፈርቱን የሚያሟሉ እንዲሆን የሚችለውን ሁሉ ያደርጋል፤

7.14. የዕጩዎችን ጥቆማ መቀበሉን ካጠናቀቀ በኋላ ለምርጫ የሚቀርቡትን ለመለየት ከጉባኤው ወጣ ብሎ አጭር ጊዜ ወስዶ በመመካከር ሊወስን ይችላል፡፡

7.15. በቅደም ተከተል በቅድሚያ ተደማጭነት በሌላቸዉ ባለአክሲዮኖች የተጠቆሙ ዕጩዎችን፣ በመቀጠል በሁሉም ባለአክሲዮኖች የተጠቆሙ ዕጩዎችን፣ በመጨረሻም ገለልተኛ የሆኑ ዕጩ ዳይሬክተሮችን ስም ዝርዝርና እንደአስፈላጊነቱ የትምህርት ደረጃ እና የሥራ ልምድ ለባለአክሲዮኖች ያቀርባል፤ ወይም በኤሌክትሮኒክ የማስታወቂያ ሰሌዳ ያሳያል፡፡

## 8. ሥራ ላይ ያሉ የቦርድ አባላት ዳግም መመረጥ

8.1. አንድ የቦርድ አባል ራሱን ወይም ሌላውን በመወከል ከስድስት ተከታታይ ዓመታት በላይ ለሆነ ጊዜ የቦርድ አባል ሆኖ ሊያገለግል አይችልም፡፡ ስድስት አመትና ከዚያ በላይ አገልግሎ የወጣ የቦርድ አባል ከስድስት ተከታታይ ዓመታት ቆይታ በኋላ እንደገና መወዳደርና መመረጥ ይችላል፡፡

8.2. በአንቀጽ 8.1 የተደነገገው ቢኖርም ጠቅላላ ጉባኤው የቦርድ ቀጣይነት (Continuity in the Board) እንዲኖር ከፈለገ በሥራ ላይ ካሉትና ለስድስት ተከታታይ ዓመታት ካገላገሉት የቦርድ አባላት መካከል ከጠቅላላው የቦርድ አባላት ቁጥር እስከ 1/3ኛ የሚሆኑትን ለተጨማሪ አንድ የአገልግሎት ጊዜ (ሶስት ዓመታት) እንዲያገለግሉ ሊመርጥ ይችላል፡፡ እንደዚሁም ስድስት አመትና ከዚያ በላይ አገልግሎ የወጣ የቦርድ አባል ከስድስት ተከታታይ ዓመታት ቆይታ በኋላ እንደገና መወዳደርና መመረጥ ይችላል፡፡

## 9. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት የምርጫ ሒደት

9.1. ኮሚቴዉ በተቻለ መጠን ዕጩዎቹ ለጠቅላላው ጉባኤዉ ራሳቸውን ባጭሩ እንዲያስተዋውቁ እና የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል ሆነው ለመሥራት ያላቸውን ፍላጐት እንዲገልጹ ዕድል ይሰጣል፡፡

9.2. ኮሚቴው የድምፅ መስጫ ወረቀት መሰራጨቱን አረጋግጦ ባለአክሲዮኖች የተሰጣቸው የድምፅ መስጫ ካርዶች/ወረቀት በመጠቀም ድምጽ እንዲሰጡ ያደርጋል። የድምፅ መስጫ ወረቀቱ ቢያንስ ፡-

9.2.1. የባለአክሲዮኑን ስም፣

9.2.2. ባለአክሲዮኑ በባለቤትነት የያዛቸውን አክሲዮኖች ብዛት፤

9.2.3. ድምጽ የሚሰጥበትን ምድብ የሚያመለክት፣

9.2.4. የባንኩን ስም፣ አርማና ማህተም፣ እና

9.2.5. ባለአክሲዮኑ ሊመርጣቸው የሚፈልጋቸውን ዕጩዎች ስም የሚፅፍበትን እና የሚፈርሙበትን ስፍራ የያዘ መሆን አለበት፡፡

9.3. የድምጽ አሰጣጡ ወይም የቆጠራው ሂደት በቴክኖሎጂ ታግዞ እንዲከናወን ሊደረግ ይችላል፡፡

9.4. ድምጽ የሚሰጠው በእያንዳንዱ ምድብ ሥር ለተመዘገቡ ዕጩዎች ሆኖ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ መሠረት ለምድቡ ድምጽ መስጠት የሚችሉ ባለአክሲዮኖች እንዲሰጡ በማድረግ ሲሆን ይኸውም፡-

9.4.1. ምድብ 1 ተደማጭነት በሌላቸዉ ባለአክሲዮኖች ብቻ፣

9.4.2. ምድብ 2 ሁሉም የባንኩ ባለአክሲዮኖች በጋራ፣

9.4.3. ምድብ 3 ሁሉም የባንኩ ባለአክሲዮኖች በጋራ፣ ድምጽ እንዲሰጡ በማድረግ ይሆናል፡፡

9.5. ባለአክሲዮኖች በድምፅ መስጫ ወረቀቶቹ ላይ ሊመርጧቸው የሚፈልጓቸውን እጩዎች ስሞች በመፃፍ ለምርጫው በተዘጋጁት ሳጥኖች ውስጥ ያስገባሉ፡፡

9.6. አንድ ባለአክሲዮን የራሱን አክሲዮን ጨምሮ ከባንኩ የተፈረመ ካፒታል ከ10% (አስር በመቶ) በላይ የሚሆነውን አክሲዮን በባለቤትነት የያዙ ባለአክሲዮኖችን ወክሎ ድምፅ መስጠት አይችልም፡፡

9.7. የቦርድ አባላት እና የባንኩ ሠራተኞች ሌሎች ባለአክሲዮኖችን ወክለው ድምጽ መስጠት አይችሉም፡፡

## 10. የምርጫ ድምፅ ቆጠራና ውጤት ስለማሳወቅ

10.1. የድምፅ አሰጣጥ ሂደቱ ከተጠናቀቀ በኋላ ኮሚቴው ድምፆቹን ይቆጥራል፡፡ እንደ አስፈላጊነቱ ድምፅ ቆጠራውን በዲጂታል ሲስተም እና በማህበሩ ፀሐፊ እና/ወይም በድጋፍ ሰጭ ሠራተኞች በመታገዝ ያከናውናል፡፡

10.2. ኮሚቴው ለእያንዳንዱ እጩ የተሰጠውን ድምፅ ብዛት እና ውድቅ የተደረጉ ድምጾችን ብዛት ይመዘግባል፤ ድምፆቹ ውድቅ የተደረጉበትን ምክንያት ጽፎ ይይዛል፡፡

10.3. አንድ ድምፅ መስጫ (ወረቀት) ውድቅ የሚደረገው ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ሁኔታዎች ብቻ ይሆናል፡፡

ሀ) የባለአክሲዮኑን ስም ያልያዘ ከሆነ፣

ለ) ባለአክሲዮኑ በባለቤትነት የያዛቸውን አክሲዮኖች ብዛት የማይገልፅ ከሆነ፣

ሐ) የድምፅ መስጫ ወረቀቱ የባንኩን ስም፣ አርማ እና ማህተም ካልያዘ፣

መ) የዕጩ ስም ካልተፃፈበት፣

ሠ) ፊርማ ከሌለበት፣

ረ) ስርዝ ድልዝ ያለው ሆኖ የማይነበብ ወይም በግልፅ እርማት ያልተደረገለት ሆኖ ከተገኘ፣

በ) በድምጽ መስጫው ላይ ምንም ነገር ያልተጻፈበት ሆኖ ከተገኘ።

10.4. ከእያንዳንዱ ምድብ የሚመረጡት የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ቁጥር ከጠቅላላ የቦርዱ ቁጥር 1/3ኛ ይሆናል።

10.5. የድምፅ ቆጠራው ሒደት ከተጠናቀቀ በኋላ ኮሚቴው የድምፅ ቆጠራውን ውጤት በቅደምተከተል፤

10.5.1. ከምድብ 1 ተደማጭነት በሌላቸዉ ባለአክሲዮኖች የተመረጡትንና በተጠባባቂነት የሚያዙትን ስም ዝርዝር ከነውጤታቸው፤

10.5.2. ምድብ 2 በሁሉም ባለአክሲዮኖች የተመረጡትንና በተጠባባቂነት የሚያዙትን ስም ዝርዝር ከነውጤታቸው፤

10.5.3. ምድብ 3 ገለልተኛ ዳይሬክተር ሆነው በሁሉም ባለአክሲዮኖች የተመረጡትንና በተጠባባቂነት የተያዙትን ስም ዝርዝር ከነውጤታቸው፤ በመግለጽ ለጉባኤው ያሳውቃል።

10.6. ከአንድ በላይ የሆኑ እጩዎች እኩል ድምፅ ያገኙ እንደሆነ አስመራጭ ኮሚቴው በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ መሠረት የቁልፍ ሙያዎች ስብጥር እንዲኖር ለማስቻል የመመረጥ እድል ላላገኘ (ላልተመረጠ) ሙያ ቅድሚያ ይሰጣል።

10.7. ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑና ተመሳሳይ ሙያ ያላቸው ዕጩዎች እኩል ድምጽ ካገኙ ለሴት ዕጩ ቅድሚያ ይሰጣል። ሆኖም እኩል ድምጽ ያገኙት ዕጩዎች ጾታ ተመሳሳይ ከሆነ ኮሚቴው የበለጠ የሥራ ልምድ ላለዉ ዕጩ ቅድሚያ ይሰጣል። በእነዚህ መስፈርቶች ተመራጩን መለየት ካልተቻለ የዚህን የአሰራር ደንብ ዓላማ በማይቃረን መልኩ ኮሚቴው ተመራጩን ይለያል።

10.8. ሴት ዕጩዎች የሚያስመርጥ ድምጽ አግኝተው መመረጥ ካልቻሉ፤ ኮሚቴው በቦርዱ ውስጥ የሚኖረው ዝቅተኛው የሴቶች ቁጥር እንዲሟላ ለማድረግ ከሴት ዕጩዎች መካከል የተሻለ ድምጽ ያመጡ ሴቶች የቦርድ አባል እንዲሆኑ ይደረጋል።

10.9. የድምጽ ቆጠራ ውጤት የተመዘገበበትን ሰነድ (ቅጽ) እና የኮሚቴው ቃለ ጉባዔ የኮሚቴው አባላት ፈርመውበት ካረጋገጡ በኋላ የጉባኤው ፀሐፊ ተቀብለው የምርጫ ውጤቱን የጉባኤው ቃለ ጉባኤ ውስጥ እንዲያካትቱት

ይደረጋል፡፡

10.10. የተቆጠሩት ድምፆች ለብቻ ይያዛሉ፡፡ ድምጽ የተሰጠው ወይም ቆጠራ የተከናወነው በቴክኖሎጂ በመታገዝ ከሆነ የቆጠራውን አጠቃላይ ውጤት የያዘ ሰነድ ታትሞና የኮሚቴው አባላት እንዲፈርሙበት ተደርጎ እንዲያዝ ይደረጋል፡፡

10.12. የድምፅ ቆጠራው ውጤት በዕለቱ ለጠቅላላ ጉባኤዉ ይገለጻል፡፡ ይህ የማይቻል ከሆነ ግን ውጤቱ በቀጣዩ የሥራ ቀን በባንኩ ዋናው መ/ቤት የማስታወቂያ ሰሌዳ እና በባንኩ ድረ ገጽ ላይ ይለጠፋል፡፡

## 11. የአስመራጭ ኮሚቴ የሥራ ማጠናቀቂያ ጊዜ

ጠቅላላ ጉባዔው የዳይሬክተሮች ቦርድ ምርጫዉን ካከናወነና የምርጫዉን ውጤት እንዳሳወቀ የተፈረመበትን ቃለ ጉባዔ እና አስፈላጊዎቹን ሰነዶች እንዳስረከበ የሥራ ጊዜው ያበቃል፡፡

# ክፍል አምስት
# ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## 12. የሌሎች ሕጎች ተፈፃሚነት

ይህንን የአሰራር ደንብ ተፈፃሚ ለማድረግ ሌሎች አግባብነት ያላቸው ሕጎች ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል፡፡

## 13. የጸደቀውን የአሰራር ደንብ ስለማክበር

ማንኛውም የባንኩ አካል ይህንን የዳይሬክተሮች ቦርድ የጥቆማ እና የምርጫ አፈጻጸም የአሠራር ደንብን በጥብቅ ተከትሎና አክብሮ የመስራት ኃላፊነት አለበት፡፡

## 14. የአሰራር ደንቡን ስለማሻሻል

ይህ የአሰራር ደንብ በማናቸውም ጊዜ በጠቅላላ ጉባዔ ውሳኔ ሊሻሻል ይችላል፡፡

## 15. ስለተሻረ የአሰራር ደንብ

ከ2015 ዓ.ም ጀምሮ ሥራ ላይ የነበረው **የባንኩ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ምልመላና ምርጫ ማስፈጸሚያ የአሰራር ደንብ**" ተሽሯል፡፡

## 16. ደንቡ የሚፀናበት ቀን

ይህ የአሠራር ደንብ በባለአክሲዮኖች በጠቅላላ ጉባኤ ከፀደቀበት ከሕዳር 11 ቀን 2018 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**ሕዳር 11 ቀን 2018 ዓ.ም**

**አዲስ አበባ**